# 181st Semiannual General Conference
## Sunday Afternoon Session, October 2, 2011

እንደገና እስክንገናኝ ድረስ

በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ይህ ከሁሉም በላይ የሚያነሳሳ ጉባኤ እንደነበረ ከእኔ ጋር እንደምትስማሙ አውቃለሁ። ልባችን ሲነኩና የዚህ መለኮታዊ ስራ ምስክራችን ሲጠናከሩ ባለፉት ሁለት ቀናት የጌታ መንፈስ በብዛት ተሰምቶናል። ጸሎት ካቀረቡት ወንድሞች በተጨማሪ፣ ለተሳተፉት እያንዳንዱ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ሁላችንም በዚህ ያለነው ጌታን ስለምናፈቅርና ልናገለግለው ስለምንፈልግ ነው። የሰማይ አባታችን ለእኛ እንደሚያስብ እመሰክራለሁ። በሁሉም ነገሮች የእርሱን እጆች አውቃለሁ።

እንደገናም መዘመሮቹ አስደናቂ ነበሩ፣ እናም ችሎታቸውን ለመካፈል ፈቃደኛ ለሆኑት የእኔንና የቤተክርስቲያኗን በሙሉ ምስጋና እገልጻለሁ።

በዚህ ጉባኤ ከአገልግሎት ለተለቀቁት ወንድሞችም ምስጋናችንን እናቀርባለን። በታማኝነት በደንብ አገልግለዋል እናም በጌታ ስራ ላይ ብዙ ነገሮችን አካፍለዋል።

ለታማኝ እና ተዳጅ አማካሪዎቼም ታላቅ ምስጋና አቀርባለሁ እናም ለደጋፊነት እና ለእርዳታ ለሚሰጡኝም አመሰግናለሁ። የጥበብ፣ የተግባር፣ ሰዎች ናቸው፣ እናም አገልግሎታቸው ታላቅ ዋጋ ያለው ነው።

ለአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድኖችም ድክመት ለማያሳዩበት በጌታ ስራ አገልግሎታቸው አመሰግናቸዋለሁ። ለሰባዎቹ ቡድኖች እና ለኤጲስ ቆጶስ አመራር ለውጤታማ አገልግሎታቸው ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንደ አጠቃላይ ደጋፊ የሚያገለግሉት ሴአትችና ወንዶችም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ወንድሞችና እህቶች፣ የሰማይ አባታችን በአለም ዛሬ ስለሚያጋጥመን ፈተናዎች እንደሚያስብ አረጋግጥላችኋለሁ። እያንዳንዳችንን ያፈቅራል እናም ትእዛዛቱን ለማክበር ስንጥርና በጸሎት እርሱን ስንፈልግ ይባርከናል።

በዳግም የተመለሰውን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ስላለን የተባረክን ነን። ከየት እንደመጣን፣ ለምን እዚህ እንዳለን፣ እና ከዚህ ህይወት ስንወጣ የት እንደምንሄድ ስለሚመለከተው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። ለህይወታችን ትርጉም አላማና ተስፋ ይሰጠናል።

እርስ በራስ ለምታገለግሉት ምስጋና አለኝ። እኛም ልጆቹን የማፍቀርና የማገልገል ሀላፊነት ያለን በምድር ላይ የእግዚአብሔር እጆች ነን።

በዎርዳችሁና በቅርንጫፋችሁ ለምታደርጉት በሙሉ ምስጋና አለኝ። በተጠራችሁበት በማንኛውም ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆናችሁ ምስጋና አቀርባለሁ። እያንዳንዱም የጌታ ስራን ወደፊት በመግፋት አስፈላጊ ነው።

ጉባኤውአሁን አልቋል። ወደ ቤታችን ስንመለስ፣ በደህንነት እንድረስ። በሌላችሁበት ጊዜ ሁሉምነገሮች ደህና ሆነውይጠብቋችሁ። በዚህ የተሰማን መንፈስም በየቀኑ የምናደርገውን ስናከናውን ከእኛ ጋር ይሁን። እርስ በራስ በተጨማሪ ደግ እንሁን። ሁልጊዜም የጌታን ስራ ስናከናውን እንገኝ።

የሰማይ በረከቶች ከእናንተ ጋር ይገኝ። ቤታችሁ በስምምነትና በፍቅር ይሞላ። ከጠላት እንዲጠብቋችሁ፣ ምስክራችሁን ሁልጊዜም አሳድጉ።

እንደ ትሁት አገልጋያችሁ፣ የእግዚአብሔርን ፍላጎት ለማሟላት እና እርሱንና እናንተን ለማገልገል በልቤ መሉ ፍላጎቴ ነው።

እወዳችኋለሁ፤ እጸልይላችኋለሁ። በጸሎታችሁ እኔንና አጠቃላይ ባለስልጣኖችን እንድታስታውሱ እንደገና እጠይቃችኋለሁ። ይህን አስደናቂ ስራ ወደፊት በመግፋት እኛ አንድነን። ሁላችንም በዚህ ተሳታፊ እንደሆንን እና እያንዳንዱ ወንድ፣ ሴትና ልጅ የሚያደርጉት ሀላፊነት እንዳላቸው እመሰክራለሁ። ሀላፊነታችንን በደንብ እንድናሟላ እግዚአብሔር ጥንካሬና ችሎታ ይስጠን።

ይህ ስራ እውነት እንደሆነ፣ አዳኝ ህያው እንደሆነ፣ እናም ቤተክርስቲያኑን እንደሚመራ እመሰክራለሁ። የዘለአለም አባታችን እግዚአብሔር ህያው እንደሆነና እንደሚያፈቅረን ምስክሬን እሰጣችኋለሁ። እርሱ በእርግጥም አባታችን ነው፣ እናም እርሱም እውነተኛ ነው። ወደ እኛ ለመቅረብ እንዴት ፈቃደኛ እንደሆነ፣ እኛን ለመርዳት ምን ለማድረግ ፈቃደኛ እንደሆነ፣ ምን ያህል እንደሚያፈቅረን፣ እና ምን ያህል እንደሚያደርግና ምን ለማድረግ ፈቃደኛ እንደሆነ ይግባን።

ይባርካችሁ። ቃል የገባው ሰላም አሁን እናም ሁልጊዜም ከእናንተ ጋር ይሁን።

በሚቀጥለው ስድስት ወር እንደገና እስክንገናኝ ድረስ ደህና ሁኑ፣ እናም ይህን የማደርገው በአዳኛችንና በቤዛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።